# የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ እና ልጅዎ



ከ 2009 ዓ.ም ጀምሮ በሚኖሩ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ሁሉም የሜሪላንድ ተማሪዎች፣ ለምረቃ ይበቁ ዘንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማን ማለፍ እንደሚኖርባቸው የክፍለ-ግዛቱ የትምህርት ቤቶች ቦርድ በሰኔ ወር ላይ ወስኗል። በዚህ ገጽና በቀጣዮቹ ጥቂት ገጾች ላይ የሰፈሩት ጥያቄና መልሶች፣ የቴስቲንግ መርሀ-ግብሩን (ፕሮግራሙን)ና ይህም በልጅዎ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ ያብራራሉ። ለጥያቄዎችዎ የሚሆኑ መልሶችን በዚህ ውስጥ ተካተው ካላገኟቸውም፣ ከልጅዎ መምህር ወይም ርዕሰ-መምህር እርዳታ ይጠይቁ። እንደዚሁም፣ የሜሪላንድ የትምህርት ክፍል ድረ-ገጽ/ዌብ-ሳይት - www.MarylandPublicSchools.org - ጥሩ የመረጃ ምንጭ ነው።

## የሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማዎች ምንድን ናቸው?

የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ግምገማዎች፣ ወይም HSA አራት ቴስቶች ናቸው—በእያንዳንዱ ቴስት አንድ የ10ኛ ክፍል እንግሊዝኛ ቴስት፣ አልጀብራ/የዳታ ትንተና፣ ባዮሎጂ፣ እና ስነ-መንግስት። ልጅዎ ኮርሱን እንዳጠናቀቀ ወይም እንዳጠናቀቀች፣ እያንዳንዱን ቴስት ይወስዳል/ትወስዳለች። ቴስቱም የምርጫ ጥያቄዎችንና በጽሁፍ የሚመለሱ ጥያቄዎችን ይይዛል።

HSA፣ ልጅዎ በኮርሱ ላይ የተማረውን/የተማረቿውን ሁሉንም አጠቃሎ ሊመዝን ስለማይችል፣ የተሟላን የኮርስ ይዘት በሚመለከት የበለጠ ለመረዳት የልጅዎን መምህር ማነጋገር ይኖርበዎታል።

## ናሙና የቴስት ጥያቄዎችን ከየት ማየት እችላለሁ?

የሜሪላንድ የትምህርት ክፍል፣ ከየትምህርት ዓይነቱ አንድ ግምገማ በየዓመቱ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል። እነዚህን ቴስቶች ተመልክቶ ለመገምገም፣ ወይም በኢንተርኔት መስመር ያን-ላይን ቴስቱን ለመውሰድ ከፈለጉም፣ www.MarylandPublicSchools.org ን ይጎብኙ። Testing/High School Assessment/HSA Test Items ከሚለው ላይ ይጠቁሙ። የ10ኛ ክፍል እንግሊዝኛ ግምገማዎች በፎል 2005 ላይ መለጠፍ/መሰራጨት ይኖርባቸዋል ።

*ወደ ቀጣዩ ገጽ ይዞራል*

*www.MarylandPublicSchools.org*



የሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ መመረቂያ መስፈርቶችን የሚያሳየውን ፖስተር ለማየት ይህን የዜና መጽሄት

**ገልጠው**

ይመልከቱ።



Maryland State Department of EDUCATION
Achievement Matters Most



## ልጄ ለመመረቅ ይበቃ/ትበቃ ዘንድ የግድ HSAን ማለፍ አለበት/አለባትን?

የዚህ ጥያቄ መልስ፣ ልጅዎ የሚመረቀው/የምትመረቀው መቼ ነው በሚለው ላይ ይወሰናል።

### ከ2009 ዓ.ም በፊት የሚመረቅ ተማሪ

የለም። ከ2009 ዓ.ም በፊት ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚመረቁ ተማርዎች፣ ለመመረቅ HSAን ማለፍ የግድ አይሆንባቸውም። ሆኖም ግን ቴስቶቹን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፣ ከዚያም በተጨማሪ፣ የወደፊት ቀጣሪዎች እና የኮሌጅ ኦፊሴሎች፣ በመቅጠርና ተማሪዎችን በመቀበሉ ሂደት ላይ ለሚያሳልፉት ውሳኔ ይረዳቸው ዘንድ የተማሪዎቹ ውጤቶች በከፍተኛ ሁለተኛ ደስርጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕታቸው ላይ እዲሰፍር ይደረጋል።

### በ2009 ዓ.ም ወይም ከዚያ በኋላ ለሚመረቁ ተማሪዎች

አዎ። በ2009 ወይም ከ2009 ዓ.ም በኋላ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሚመረቁ ተማሪዎች ለመመረቅ ይችሉ ዘንድ HSAን ማለፍ የግድ ይሆንባቸዋል፡

- አራቱንም HSA በሙሉ ማለፍ። የማለፊያ ማርኮችም፣ አልጀብራ/የዳታ ትንተና፥ 412፣ ስነ-መንግስት፥ 394፣ እና ባዮሎጂ፣ 400 ናቸው። የ10ኛ ክፍል እንግሊዝኛ የማለፊያ ውጤት መጠንም በፎል 2005 ይወሰናል።

*ወይም*

- በመንግስት ተቀባይነት ባላቸው ምትክ ቴስቶች የማለፊያ ውጤት በማግኘት ከነዚህም ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑትን ለHSA ማለፊያ ውጤት ማተካካት። ተቀባይነት የሚኖራቸው ምትክ ቴስቶችንም ግዛታዊ-መንግስቱ ገና መምረጥ ይኖርበታል፣ ከሚመረጡት ውስጥም የላቀ ምደባና ዓለም አቀፍ የባችለር ድግሪ ቴስቶች ሊካተቱ ይችላሉ።

*ወይም*

- በእያንዳንዱ ቴስት ዝቅተኛ የሚባለውን ውጤት ማግኘትና ውጤቶቹ ሲጤቃለሉም ከአራቱ የHSA ማለፊያ ውጤቶች ጋር እኩል የሚሆን ውጤትን ማግኘት። የግዛታዊ መንግስቱ የትምህርት ቦርድ ዝቅተኛውን የመነሻ ውጤት መጠን ገና አልወሰነም፣ ሆኖም ግን ከማለፊያ ውጤቶቹ የሚያንስ ነው የሚሆነው። ይህ የሚጠቃለል ውጤት አማራጭም ልጅዎ በአንዱ ቴስት ዝቅተኛ፣ በሌላኛው ደግሞ ክፍተኛ ውጤቶችን በማስመዝገብ ውጤቱን ለማመጣጠን እንዲችል/እንድትችል ይረዳዋል/ይረዳታል።

ሁሉም ተማሪዎች—ከ2009 ዓ.ም በፊትም ሆነ በኋላ የሚመረቁ ሁሉ—የግዛቱን የክሬዲት መጠን፣ የአገልግሎት ትምህርትን፣ እና አስፈላጊውን የክፍል ውስጥ ክትትል፣ እንደዚሁም ደግሞ በትምህርት ቤትዎ የሚጣለውን ማንኛቸውንም ዓይነት አስፈላጊ ጉዳዮች ሁሉ ማሟላት ይኖርባቸዋል። የሜሪላንድ የምረቃ ሁኔታን በተጠቃለለ መልኩ የሚያሳየውን ፖስተር ለመመልከት ይህን የዜና መጽሄት ገልጠው ይመልከቱ።

## ልጄ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ሲሆን/ስትሆን አሁን ግን አልጀብራን እየወሰደ/እየወሰደች ነው። ሥለዚህ ለመመረቅ የአልጀብራ HSAን ማለፍ ይኖርበታል/ይኖርባታል?

አዎ። ተማሪዎች ኮርሶችን ካጠናቀቁ በኋላ እያንዳንዱን HSA ይወስዳሉ። ልጅዎ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማር ሆኖ/ሆና ነገር ግን ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሚመጥኑ ኮርሶችን እየወሰደ/እየወሰድች ከሆነ – ይህ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከአልጀብራ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው – ለመመረቅ ይችል/ትችል ዘንድ ተገቢውን HSA ማለፍ ይኖርበታል/ይኖርባታል። በእርግጥ አንድ ተማሪ ቀደም ብሎ HSAን ቢወስድ፣ HSAን ለማለፍ ሰፋ ያለ ዕድል እንዲኖረው/እንዲኖራት ያደርጋል።

## ይህም ሆኖ፣ ልጄ የሜሪላንድ ተግባራዊ ቴስትን የማለፍ ግዴታ ይኖርበታል/ይኖርባታልን?

የለም። የሜሪላንድ ተግባራዊ ቴስትን HSA ተክቶታል። HSAን ማለፍ ግዴታ የሚሆንባቸው የመጨረሻዎቹ ተማሪዎች በ2004 ዓ.ም የሚመረቁት ነበሩ። ሆኖም ግን፣ ተግባራዊ ቴስቶች ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች አዘውትረው ይሰጡ ነበር፣ ስለሆነም ልጅዎ/ልጆችዎ ከመቋረጣቸው በፊት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ተግባራዊ ቴስቶችን ወስደው ሊሆን ይችላል።

## ግዛታዊ-መንግስቱ የተግባር ቴስቶችን እና በኮምፒውተር መረብ (ዖን-ላይን) የሚሰጡ ኮርሶችን እየቀረጸ ነው፡፡

ተግባራዊ ቴስቶች፣ መሰረታዊ ችሎታዎችን ለመለካት ሲባል በ1980ዎቹ የተፈጠሩ ነበሩ፡፡ ነገር ግን፣ የተሳካ ሕይዎትን ለመቀዳጀት ደግሞ፣ ከመሰረታዊ ችሎታዎች ግንባታ ባሻገር ብዙ የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ኮሌጆችና የስራ ቀጣሪዎች፣ ተማሪዎች የበለጠ እንዲያውቁና ቀደም ሲል ከነበሩበት ሁኔታ በጣም በተሻለ ደረጃ ሊሰሩ የሚችሉ እንዲሆኑ ይጠብቃሉ፡፡ የህዝብ ት/ቤቶችም ተማሪዎችን ለዚህ ከፍተኛ ራዕይ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣ HSAም የዚህ ተማሪዎችን የማዘጋጀቱ ሂደት አስፈላጊው አካል ነው፡፡

### የልጀን ውጤት የማየው መቸ ነው?

ቴስቱ ከተሰጠ በግምት ከዘጠኝ ሣምንታት በኋላ፣ ግዛታዊ-መንግስቱ ሁሉንም የተማሪዎች ውጤቶች ለየትምህርት ቤቶቻቸው ወረዳዎች ይልካል፡፡

### ልጄ ለHSA እንዴት ነው መዘጋጀት የሚኖርበት/የሚኖርባት?

የክፍል ደረጃዎችንና ውጤቶችን ለማበረታታት ሲባል ለሚሰጡ የዘወትር የክፍል ውስጥ ቴስቶች ከሚደረጉ ዝግጅቶች ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ልምምድና ጥናት ማድረግ - የኮርሱን የክፍልና የቤት ስራ አዘውትሮ መከታተልና መስራት፣ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ፣ በርትቶ ማጥናት - ተማሪዎችን ለHSA ይረዳቸዋል፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ደግሞ ተማሪዎች ለHSA እራሳቸውን ለማዘጋጀት የሚችሉባቸው ሌሎች መንገዶች ናቸው፡፡

### በዝግጅትና የጥናት ዘዴ ላይ ማትኮር

በHSA የሚሸፈኑ አጠቃላይ የኮርስ ይዘቶች ላይ በማትኮር፣ ይህም ተማሪዎች በዓመቱ ውስጥ የተማሩባቸውን ጠቅላላውን ማስታዎሻዎቻቸውን እና በየትምህርት ምዕራፉም የተጠቃለሉትን የትምህርት ይዘቶች በሙሉ በሚገባ ዝግጁ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### የመጻፍ ችሎታን ይበልጥ ማሳደግ/ማዳበር

የተወሰኑ የHSA ክፍሎች የጽሁፍ ምላሽን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ከተመረቁ በኋላ የሚኖራቸው እቅድ ምንም ይሁን ምን፣ በደንብ መጻፍ የሚችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

### ጊዜን በአግባቡና በጥንቃቄ መጠቀም

አንድ የጥናት ግኝት እንዳመለከተው፣ ግሩም የሆነ የጊዜ አጠቃቀም ስልት፣ ከSAT (የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቴስት) ውጤቶች ይልቅ በጣም በተሻለ ሁኔታ የኮሌጅ ውጤትን ለማግኘት እንደሚረዳ ይተነብያል፡፡

### ለሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ ከልብ መሆን/ተገቢውን ትኩረት መስጠት

በክፍሎች 3-8 እና በክፍል 10 የሚሰጥ የሜሪላንድ የትምህርት ቤት ግምገማ፣ ለHSA ጥሩ ልምምድ ነው፡፡

### ልጄ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቴሶችን ባያልፍ/ባታልፍስ?

ልጅዎ HSAን ካላለፈ/ካላለፈች፣ በዚያ የትምህርት ዓይነት ላይ ተጨማሪ እገዛ እንዴት ማግኘት እንደሚችል/እንደምትችል የበለጠ ሊያብራሩልዎት የሚችሉትን መምህሩን/መምህሯን በማግኘት ያነጋግሩ፡፡ ለጅዎም የትምህርት ዓይነቱን ይዘቶች አንዴ ከከለሰ/ከከለሰች እና ተጨማሪ እገዛዎችን ካገኘ/ካገኘች በኋላ፣ ቴስቱ በሚሰጥበት ቀጣይ ወቅት ላይ እንደገና ቴስቱን ሊወድ/ልትወስድ ይችላል/ትችላለች፡፡ (ቴስቶችን እንደገና መውሰድ የሚፈልጉ ተማሪዎች በአመት ሦሥት ጊዜ ይህንኑ ማድረግ ይችላሉ - በጃኑዋሪ፣ በሜይ እና በበጋው/ሰመር ወቅት ማለት ነው፡፡)

የሜሪላንድ ግዛታዊ-መንግስት፣ ተጨማሪ እገዛ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን ለመለየት፣ የወረዳ ት/ቤቶች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን የተግባር ቴሶች በማዘጋጀት ላይ ነው፡፡ ወረዳዎችም ÷ ተማሪዎች HSAን ከመውደቃቸው

*ወደቀጣዩ ገጽ ይዞራል*



## የሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማዎችን ለሚመለከት የበለጠ መረጃ

**www.MarylandPublicSchools.org**

በገጹ ራስጌ ላይ ካለው የቴስቲንግ ዝርዝር ላይ፤ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ የሚለውን ይምረጡ።

በፊት ያንን ዓይነቱን እገዛ ለተማሪዎች ሊያቀርቡ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም፤ ግዛታዊ-መንግስቱ፤ ተማሪዎችን ለቴስቱ ዝግጁ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ባለ-ኮምፒውተር መረብ (ዖን-ላይን) ኮርሶችንም እያዘጋጀ ነው። እነዚህ ኮርሶች በሴፕቴምበሯ 2005 ላይ ዝግጁ ሆነው ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይገመታል።

### ልጄ በቴስቱ ወቅት ባይገኝ/ባትገኝስ?

በመደበኛ የHSA ቴስት ወቅት ላይ ያልተገኙ ተማሪዎች የማካካሻ ቴስቶችን ለመስጠት ከሚታቀዱት ቀናት ውስጥ በአንዱ ቀን ሊወስዱ ይችላሉ። (እነዚህ ቀናትም መቸና መቸ እንደሚሆኑ የልጅዎ መምህር ወይም ርዕሰ-መምህር ሊነግሩዎት ይችላሉ)። ልጅዎ ካልታመመ/ካልታመመች በስተቀር፤ ቴስቱ በሚሰጥበት ወቅት በትምህርት ቤት ለመገኘት አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል/ይኖርባታል።

### የጤና/የአካል ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎች፤ ለመመረቅ HSAን ማለፍ የግድ ይሆንባቸዋልን?

በ2009 ዓ.ም ላይ ከሚጀመሩ ክፍሎች ጀምሮ፤ ሁሉም ተማሪዎች—ልዩ ትምህርት የሚቀበሉ ተማሪዎችንም ጨምሮ—በድፕሎማ ለመመረቅ ይቻላቸው ዘንድ HSAን ማለፍ የግድ ይሆንባቸዋል። በዚህ ወቅት፤ የጤና/የአካል ጉድለት ላለባቸው ተማሪዎች የሚሆን አማራጭ የመመረቂያ ቴስቶች አይኖሩም። ሆኖም ግን፤ በነባሩ የቴስት ዓይነቶች ላይ ችግር ለነበረባቸው ተማሪዎች መንግስት እንዴት አማራጭ ግምገማዎችን ሊያዘጋጅ እንደሚችል ሊያመላክት የሚችል አንድ ጊዜያዊ የተግባር ኮሚቴ ሁኔታውን በዚህ የፎል (መከር) ወቅት ላይ ማጥናት ይጀምራል። አማራጭ ግምገማዎቹም፤ ልክ የHSA ይዘቶችን የሚያካትቱ ሲሆን፤ ነገር ግን በተለይ የአካል/ጤና ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎችን የበለጠ የሚያግዙ ይሆናሉ። የተግባር ኮሚቴው የመፍትሄ ሃሳብም በፎል (መከር) 2007 ላይ ይፋ ይሆናል።

ልዩ ትምህርት የሚከታተሉ በርካታ ተማሪዎች፤ በትምህርት አሰጣጡና በቴስት ወቅት የሚያስፈልጓቸውን የእገዛ ዓይነቶች እየመዘገበ የሚያስቀምጥ በየግላቸው የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) አላቸው። የሜሪላንድ የትምህርት ክፍል፤ ትምህርት አቀራቢዎች ለነዚህ ዓይነቶቹ ተማሪዎች በክፍለ-ግዛታዊው ቴስት ወቅት ሊያደርጉ ስለሚገባቸው የእርዳታ ዓይነቶች ለመወሰን የሚረዷቸውን ሁኔታዎች የሚዘረዝር መመሪያ ያሳትማ። *እርዳታን መለገስ አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች፤ በቂ ምክንያቶች፤ እና ከሜሪላንድ የግምገማ መርሃ-ግብሮች (ፕሮግራሞች) ተማሪዎችን ነጻ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን የሚያብራራው መመሪያ* (*Requirements for Accommodating, Excusing, and Exempting Students in Maryland Assessment Programs)* በድረ-ገጽ (ዌብ) www.MarylandPublicSchools.org. ላይ ይገኛል። [ዲቪዚዮኖች/ልዩ ትምህርት እና ቅድመ እርዳታ/ህትመቶች እና ዘገባዎች (ሪፖርቶች) (Divisions/Special Education and Early Intervention/Publications and Reports).] ከሚሉት ላይ ክሊክ ያድርጉ፤ እንደዚሁም ደግሞ፤ የልጅዎ መምህር ወይም ርዕሰ-መምህር ለክፍለ-ግዛታዊው ቴስት የሚፈቀዱ የእገዛ ዓይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ሊያብራሩለዎት ይችላሉ።

ከፍተኛ የጤና/የአካል ጉድለት ያለባቸው እጅግ በጣም አነስተኛ ተማሪዎች ብቻ በድፕሎማ ምትክ የፕሮግራም ፍጻሜ ሰርቲፊኬት ሊያገኙ ይችላሉ። ከጤና/የአካል ጉድለት ጋር ለሚኖሩ ተማሪዎች የሚሰጠው ይህ የፕሮግራም ፍጻሜ ሰርቲፊኬት፤ ለረዥም ዓመታት የነበረ ሲሆን፤ አሁን በቅርብ ወቅት በሜሪላንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምረቃ ፖሊሲ ላይ በተደረገ መሻሻል ምክንያት የመጣ ለውጥ አይደለም።

ልጅዎንና የሚከታተለውን/የምትከታተለውን መርሀ-ግብር (ፕሮግራም) የሚመለከቱ ምጥን ጥያቄዎች ካሉዎት፤ የልጅዎን መምህር ወይም የIEP ቡድኑን ያነጋግሩ። ■

## የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ እና ልጅዎ

**የአካደሚክ ፖሊሲ ቢሮ።**

Ronald A. Peiffer
የግዛታዊ ትምህርት ቤቶች ምክትል የበላይ ኃላፊ

Edward L. Root
ፕሬሲደንት፤ ግዛታዊ የትምህርት ቦርድ

Nancy S. Grasmick
ጸሃፊ- የቦርዱ የንብረት ክፍል፤
ግዛታዊ የትምህርት ቤቶች የበላይ ኃላፊ

Robert L. Ehrlich, Jr., ገዢ

Maryland State Department of Education • 200 West Baltimore Street • Baltimore, Maryland 21201-2595
ሥልክ: 410.767.0600 or 888.246.0016 • TTY/TDD (ለደንቆሮዎችና የመስማት ችግር ላለባቸው): 410.333.3045 • ፋክስ: 410.333.2275 •
www.MarylandPublicSchools.org